

9

# አፈግፋጊ (ኤሰንስ)

## 9-1

### ኤሰንስና ታሪካቸው

በክርስቶስ ዘመን ከነበሩት ስድስት ዋና ዋና የሃይማኖች እንቅስቃሴዎች መካከል በአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ ታሪካቸው በግልጽ ያልተጠቀሰ ኤሰንስ የተባሉት ክፍሎች ናቸው። ስለኤሰንስ ታሪክ በግልጽ የታወቀው ከጥንታዊ ጽሁፎች (ዴድ ሲ ስክሮል) ላይ በተደረገው የጥናት ትኩረትና፥ ኪብረት ኩምራን የተባለው ጥንታዊ የገዳም ፍርስራሽ ውስጥ በተገኘው አንዳንድ ሁኔታዎችና መግለጫዎች ነበር። አብዛኛዎቹ ኤሰንሶች ከሮም ጋር በነበረው ጦርነት ምክንያት ያለቁ ሲሆን ጥቂቶቹ ደግሞ ወደ ክርስትና እምነት እንደመጡ ታሪክ ይናገራል። እነዚህ ክፍሎች እምነታቸው ከአይሁድ የኃይማኖት ክፍል ውስጥ ይሁን እንጂ ብዙ ሥርዓታቸው ከሌሎች አይሁዶች የተለዩ ናቸው።

### የኤሰንስ አኗኗር

ኤሰንስ የሚኖሩት ገዳም ውስጥ በማኅበር ሲሆን ኅብረቱን የሚያስተዳድር አንድ የበላይ ጠባቂ ወይንም መሪ አላቸው። አባላቱ መሪ ለሆነው ሰው ፍጹም የሆነ አክብሮትና ታዛዥነት ግዴታቸው እንደሆነ አስቀድመው ያውቃሉ። ማንኛውም አባል ለመሆን የሚፈልግ የውጪ ሰው፥ አባል ከመሆኑ በፊት የሚያልፍባቸው ሁለት ደርጃዎች አሉት። በመጀመሪያ ደርጃ የሰውየው አቋምና ይዞታ ለአንድ ዓመት ያህል ይመረመራል። የመጀመሪያውን ድረጃ ካለፈ ሙሉ አባል ሳይሆን ተጨማሪ ሁለት ዓመት በገዳሙ ውስጥ ይቆያል። በጠቅላላው ሶስት ዓመት ተመርምሮ ብቁ ሆኖ ከተገኘ አባል እንዲሆን ይፈቀድለታል። አባልም የሚሆነው የገዳሙን ምስጢርም ሆነ ትምህርት አባል ላልሆነ ለውጪ ሰው እንደማይገልጽ በመሀላ ለአባላቱ ካረጋገጠ በኋላ ብቻ ነው። በሙሉ አባልነት የተቀበሉት መሆኑን የሚገልጹት የህብረት እንጀራ አብሯቸው እንዲቆርስ በማድረግ ነው። ትላልቅ ሰዎች እንጂ ልጆች አባል መሆን አይችሉም። ይሁን እንጂ በኤሰንስ ትምህርትና ሥርዓት እንዲያድጉ ልጆችም ዕድል ይሰጣቸዋል። ከማህበሩ አባላት መካከል ጥፋት የተገኘበት ሰው የቅጣት ውሳኔ የሚሰጠው በገዳሙ ውስጥ የሚገኙት ጠቅላላ አባሎች ናቸው። በሚያደረገውም ውሳኔ አባላቱ መቶ በመቶ ካልተስማሙ ውሳኔው አይጸናም። በሙሉ ድምጽ ተስማምተው ከወሰኑ ድግሞ ውሳኔአቸው በምንም ዓይንት አይለወጥም።

ከማኅበሩ እንዲወጣ የተወሰነበት ሰው ቀስ በቀስ እንዲሞት የተበየነበት እንደሆነ ይታመናል። ምክንያቱም በኤስንስ ህብረትና ትምህርት የሚያምን ሰው በሌላ ሰው እጅ የተሠራ ምግብ በምንም ዓይነት ስለማይበላ ነው። ኤሰንስ ምግባቸውና ልብሳቸው አንድ ዓይነት ነው። ኑሮአቸው ፍጹም ተራ ከመሆኑም በላይ ከውጭ ዓለም ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላቸው ራሳቸውን በገዳም ውስጥ ዘግተው የሚኖሩ ናቸው። ጋብቻን የሚቃወሙ የሥጋ ፍላጎት ኃጢአት ነው ብለው የሚያምኑ ናቸው።

በዚህ ምክንያት የራሳቸው የሆኑ ልጆች ስለሌላቸው የሌሎችን ሰዎች ልጆች ከውጪ አምጥተው ያሳድጋሉ። ምግባቸው ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ከመሆኑም በላይ ፍጹም ተራና የማይረባ ነው። የሚመገቡትም ህይወታቸውን ለጊዜ ለማቆየት ያህል ብቻ ነው። የሥጋ ምቾት ነፍስን ይጎዳል ብለው ስለሚያምኑ ራሳቸውን ከብዙ ነገር ይቆጥባሉ። የለበሱትም ልብስም ሆነ ጫማ ፍጹም ከአገልግሎት ውጪ ካልሆነ ጨርሶ አይቀይሩም። በጠቅላላው ዓለምን ሸሽተው ለብቻቸው በፍጹምነት ለመኖር የሚታገሉ ክፍሎች ናቸው። የኤሰንስ የህይወት አቋም የተመሠረተው በማፈግፈግ ላይ ነው። የዓለም ውጣ ውረድ ሥርዓትና ደንብ እንዳይነካቸው የተሸሸጉ ክፍሎች ናቸው። ራሳቸውን ቅዱስ አድርገው ለመኖር በአካል መውጣት አለብን ብለው ያምናሉ።

## የዘመኑ ኤሰንስ

በአሁንስ ዘመን እነዚህን ክፍሎች የሚመስሉ ግለሰቦች ይኖሩ ይሆን? አንደኛውን ለይቶላቸው ገዳም ውስጥ የተቀመጡትን ማለታችን አይደለም። በኀብረተሰቡ መካከል እየኖሩ የራሳቸውን ዓለም ፈጥረው ከዓለም ውጪ ነን ብለው ራሳቸውን የሚገልሉ ማለታችን ነው። ወይንም በዕለታዊ ኑሮአቸው የሚያጋጥማቸውን ትግል በአግባቡ በመግጠም ፈንታ ለማምለጥ የሚሞክሩትን ማለታችን ነው። ክርስትያኖች ሆነው ራሳቸውን ከዓለም የደበቁ ይኖሩ ይሆን?

## አማኝ ከዓለም አይወጣም

የአማኝ የእምነቱ ኃይልና ጥንካሬ የሚለካው በሕይወቱ መለወጥና አኗኗር እንጂ በአካል ከዓለም ወጥቶ በብቸኝነት በመኖር እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ ሲጸልይ "...ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም ውጪ እንድታወጣቸው አይደለም" አለ (ዮሐ. 17፥15)። ደቀመዛሙርቱ በቅድስና መኖራቸውን ቢፈልግም ከዓለም ውጪ ሆነው መኖራቸውን የተቀበለው ሃሳብ አይደለም። ለብቻቸው ተገልለው መቀመጣቸውን ሳይሆን በዓለም ውስጥ ተቀላቅለው በቅድስና መኖራቸውን ይደግፋል።

## በመሸሽ ብቻ አናሸንፍም

አማኝ ከፈተና ከትግል ህይወት ሸሽቶ በመኖር ብቻ ቅድስናን ማግኘት እንደማይችል ማወቅ አለበት። መሸሽ ያለአግባቡ ከሆነ መሸነፍ እንጂ ማሸነፍ አይደለም። እንደ ዮሴፍ ፈተናን ሸሽቶ መሄድ የሚያስፈልግበት ጊዜ ይኑር እንጂ፥ ሁልጊዜ ግን በሽሽት መኖር አይቻልም። "ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል" (ያዕ. 4፥7) ሲል ሽሽታችሁ ፈተና ከማይደርስበት ሥፍራ ተደበቁ ማለቱ እንዳልሆነ ግልጽ ነው።

## አማኝ ከአለማዊነት ይርቃል

አማኝ በዓለም ውስጥ ይኑር እንጂ፥የዓለም ኃጢአት ይሳተፋል ማለት አይደለም። የክርስትና ህይወቱን ከሚያበላሽና ከሚበርዝ ከዓለማዊነት መንፈስ ራሱን መጠበቅና በጥንቃቄ መራመድ ይገባዋል። በዓለም ያለው መንፈስ አማኞችን የሚታገል ልዩ የጠላት ኃይል ሲሆን፥ ብዙዎቹንም ወግቶ ጥሏል። ይሁን እንጂ ክርስቲያን በፍርሃትና በመርበትበት እንዲሁም በሽሽት ሳይሆን በክርስቶስ ጸጋ ውስጥ ይኖራል። ጳውሎስ "ሁሉን በሚያስችለኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ" እንዳለው፥ በዓለም ውስጥ በአሸናፊነት ለመኖር የክርስቶስ ጸጋ ያስችለዋል።

## አማኝ ብርሃኑን ይሰጣል

አማኝ ከዓለም ውጪ ራሱን ካስወጣና በድብቅ ከኖረ፥ በሕይወቱ የቅድስና አኗኗር ምን ዓይነት እንደ ሆነ በግልጽ እንዳይታይ መከልከሉ ይሆናል። አማኝ ለጨለማው ዓለም ብርሃን የሆነውን ሕይወቱን ማሳየት አለበት። በዓለም ውስጥ ያለው ሰው ምን ያህል ሕይወቱ በጨለማ ውስጥ እንዳለ ማየት የሚችለው የአማኙን ሕይወት ሲያይ ነው።

## አማኝ ለዓለም ምስክር ነው

ክርስቶስ “አንተ እኔን ወደ ዓለም እንደላክኸኝ እኔም እነርሱን ወደ ዓለም ላኩኋቸው” ይላል (ዮሐ. 17፥18) ። ክርስትያን ወደ ዓለም የተላከ መልዕክተኛ ነው። የወንጌሉን ብርሃን በሕይወቱና በቃሉ ለዓለም ይመሰክራል። ይህንን ባለመረዳት የራሱን ሕይወት ብቻ እየጠበቀ ለሌላው ግድ የሌለው አማኝ ከኤሰንስ ሕይወት ይህን ያህል የተሻለ አይደለም። በክርስትና ሕይወቱ ጠንቃቃና እንከን የማይገኝበት ሕይወት ቢኖር እንኳን ከእግዚአብሔር ቃልና ትዕዛዝ ውጪ ሸሽቶ በመኖሩ የሳተ ነው። በክርስቶስ ውስጥ ያለውን ሰላምና ደስታ የሞላበትን ሕይወት የማያምኑት አይተው እንዲለወጡ የእኛን የተለወጠውን ሕይወት እናሳያቸው እንጂ እንደ ኤሰንስ ከዓለም አንሸሽ።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። እሜን!**